# መርሻ ማንነቱ

አብራሃም በየነ

ለመሠሪ ሴራው ቲፎዞ ፍለጋ
ጎንደሮችን ሲያገኝ ሊቦ ወይና ደጋ
ዕብናት ጎርጎራ ወይ ደብረታቦሬ
ለቁስ ሳይቀር ዋሽቶ ይሆናል ጎንደሬ።
ዘወር ብሎ ደግሞ ያለጥጣሬ
ጎጃሞችን ሲያገኝ ሞጣና አቸፈሬ
ጎጃሜ ይሆናል ዳንግላና ቡሬ።
መገልበጥም ሲሻ ወደ ሌላ ዘውጌ
ወሊሶ ይሆናል ጨቦና ጉራጌ።
ሌላ ጊዜ ደግሞ ሁኔታውን ቃኝቶ
ዘወር ግልብጥ ብሎ ዙሪያ ገቡን አይቶ
ጭንብሉን አውልቆ እንዳመችነቱ
ለዕውቅና ይሮጣል በኢትዮጵያዊነቱ።

ሚያዚያ 2000
abraham beyenne